የክትባት መረጃ መግለጫ

# Hib ክትባት

## ማወቅ የሚገባዎት

(ሄሞፊሊየስ
ኢንፍሉኤንዛ አይነት b)

Many Vaccine information Statements are available in Spanish and other languages. See www.immunize.org/vis

Hojas de información sobre vacunas están disponibles en español y en muchos otros idiomas. Visite www.immunize.org/vis

## 1 መከተብ ለምን አስፈለገ?

ሄሞፊሊየስ ኢንፍሉኤንዛ አይነት b (Hib) በሽታ በባክቴሪያ የሚከሰት ከባድ በሽታ ነው። ብዙውን ጊዜ ከ 5 አመት በታች ያሉ ልጆችን ያጠቃል። በተወሰነ የህክምና ሁኔታ ውስጥ ያሉ አዋቂዎችንም ያጠቃል።

ባክቴሪያው ያለባቸው ነገር ግን እንዳለባቸው በማያውቁ ልጆች ወይም አዋቂዎች አካባቢ በመገኘት ልጅዎ የ Hib በሽታ ሊይዘው ይችላል። ተሃዋስያኖቹ ከሰው ወደ ሰው ይሰራጫሉ፡ ፡ ተሃዋስያኖቹ በልጅ አፍንጫ ወይም ጉሮሮ ውስጥ የሚቆዩ ከሆነ፣ ልጁ የማይታመምበት ዕድል አለው። አንዳንድ ጊዜ ግን ተሃዋስያኖቹ በሳምባ ወይም በደም ስር ውስጥ ይሰራጫሉ፣ በመሆኑም Hib ከባድ ችግር ሊፈጥር ይችላል። ይህም ኢንቬሲቭ Hib በሽታ ይባላል።

ከ Hib ክትባት በፊት፣ Hib በሽታ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በሚኖሩ ከ 5 አመት በታች ባሉ ልጆች መካከል የባክቴሪያል ማጅራት ገትር ቀዳሚ ምክንያት ነበር። ማጅራት ገትር የጭንቅላት እና የአከርካሪ ጉዳት ነው። ወደ አእምሮ ጉዳት እና መስማት መሳን ሊያመራ ይችላል። የ Hib በሽታ እነዚህንም ሊያስከስት ይችላል፡

- የሳንባ ምች
- ለመተንፈስ በሚያስቸግር ሁኔታ በጉሮሮ ላይ ከባድ እብጠት መኖር
- የደም፣ የመገጣጠሚያ፣ የአጥንት፣ እና የልብ ሽፋን በሽታ
- ሞት

ከ Hib ክትባት በፊት፣ በየአመቱ ወደ 20,000 የሚሆኑ ከ 5 አመት በታች የሆኑ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚገኙ ልጆች የ Hib በሽታ ተጠቂ ነበሩ፣ እና ከ3% - 6% የሚሆኑት ሞተዋል።

የ Hib ክትባት የ Hib በሽታን ይከላከላል። የ Hib ክትባት አገልግሎት ላይ ከዋለ በኋላ፣ የኢንቬሲቭ Hib በሽታ ማህደር ቁጥር ከ 99% በላይ ቀንሷል። ክትባቱን ብናቆም ብዙ ልጆች የ Hib በሽታ ይይዛቸዋል።

## 2 Hib ክትባት

የተለያዩ አይነት ያላቸው የ Hib ክትባቶች ይገኛሉ። ከክትባቱ አይነት በመነሳት ልጅዎ 3 ወይም 4 ክትባት ይሰጠዋል።

የ Hib ክትባት ክትባት መጠን ብዙውን ጊዜ የሚመከሩት በእነዚህ እድሜ ነው፡

- የመጀመርያው ክትባት መጠን፡ በ 2 ወራት እድሜ
- ሁለተኛው ክትባት መጠን፡ በ 4 ወራት እድሜ
- ሶስተኛው ክትባት መጠን፡ በ 6 ወራት እድሜ (ካስፈለገ በክትባቱ አይነት በመነሳት)
- የመጨረሻው/ቡስተር ክትባት፡ በ 12-15 ወራት እድሜ

Hib ክትባት እንደሌሎቹ ክትባቶች በአንድ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።

Hib ክትባት እንደሌሎቹ ክትባቶች በአንድ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡ ፡ ቅልቅል ክትባቶች የሚሰሩት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ክትባቾች ተደባልቀው በአንድ ክትባት መልክ ሲሰጡ ሲሆን ከአንድ በላይ የሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል ይረዳል።

ከ 5 ዓመት በላይ የሆኑ ህጻናትና አዋቂዎች የ Hib ክትባት አያስፈልጋቸውም። ነገር ግን አስፕሌኒያ ወይም ሲክል ሴል በሽታ ያለባቸው ከፍ ያሉ ህጻናት ወይም አዋቂዎች ጣፊያን ለማስወገድ ወይም የአጥንት መቅኔን ለመቀየር በሚደረጉ ቀዶ ጥገናዎች ጊዜ ክትባት ይመከራል። እንዲሁም ከ 5 እስከ 18 ዓመት ያሉ በ HIV ለተያዙ ሰዎችም ይመከራል። ሀኪምዎ የበለጠ መረጃ ሊሰጥዎ ይችላል።

ሃኪምዎ ወይም ክትባቱን የሚሰጥዎ ሰው የበለጠ መረጃ ሊሰጥዎ ይችላል።

## 3 አንዳንድ ሰዎች ይህንን ክትባት መውሰድ የለባቸውም

Hib ክትባት 6 ሳምንት ላልሞላቸው ህጻናት መሰጠት የለበትም።

ከዚህ በፊት ከወሰደው ከ Hib ክትባት መጠን የተነሳ ህይወትን አደጋ ላይ የሚጥል አለርጂ የተነሳበት ወይም ከዚህ ክትባት ጋር በተያያዘ ከባድ አለርጂ አጋጥምዎ የሚያውቅ ከሆነ፣ ይህንን ክትባት አይውሰዱ። ክትባቱን ለሚሰጠው ሰው ስላለብዎት ከባድ የአለርጂክ ምልክቶች ይንገሩት።

መጠነኛ ህመም የታመሙ ሰዎች Hib ክትባትን መውሰድ ይችላሉ። ከበድ ያለ ወይም በጣም ህመም ላይ ከሆኑ ፣ እስኪሻልዎ ድረስ ቢጠብቁ ይመረጣል። ክትባቱ ሊሰጥ በታሰበበት ቀን ላይ የሚወስደው ሰው ጥሩ የጤንነት ስሜት ላይ ካልሆነ ለህክምና እንክብካቤ ሰጪዎ ይንገሩ።

U.S. Department of Health and Human Services
Centers for Disease Control and Prevention

## 4 | የክትባት አፀፋዊ ምላሽ ስጋቶች

ክትባትን ጨምሮ በሁሉም መድሀኒቶች የጎንዮሽ ጉዳት የመፈጠር እድል አለ። እነዚህ መለስተኛ ሲሆኑ በትንሽ ቀናት ውስጥ በራሳቸው የሚጠፉ ናቸው። ነገር ግን በጣም አልፎ አልፎ ቢሆንም ከባድ ህመም ሊፈጠር ይችላል።

አብዛኛዎቹ የ Hib ክትባት የሚወስዱ ሰዎች ምንም ችግር አያጋጥማቸውም።

**ከ Hib ክትባት በኋላ የሚያጋጥሙ** መለስተኛ ህመሞች:
- ክትባቱ የተሰጠበት ቦታ መቅላት፣ መሞቅ፣ ማበጥ
- ትኩሳት

እነዚህ ችግሮች የተለመዱ አይደሉም። የሚከሰቱ ከሆነ፣ ከክትባቱ ጊዜ ወዲያው ሲጀምሩ ከ 2 እስከ 3 ቀን ይቆያሉ።

**የትኛውንም ክትባት ከወሰዱ በኋላ የሚያጋጥሙ ችግሮች:**
የትኛውም መድኃኒት ከበድ ያለ የአለርጂክ አፀፋዊ ምላሽ ሊያስነሳ ይችላል። ከክትባት የሚመጡ አለርጂኮች በጣም አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ሲሆኑ ከ አንድ ሚሊዮን ክትባቶች በ 1 እንደሚከሰት ይገመታል፤ የሚከሰተቱትም ክትባቱ ከተሰጠ በኋላ ከጥቂት ደቂቃዎች እስከ ጥቂት ሰዓታት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።

ልክ እንደ ሌላው መድኀኒት፣ ክትባት በጣም ከባድ ጉዳት ወይም ሞት የሚያስከስትበት በጣም ጠባብ እድል አለ።

ተለቅ ያሉ ህጻናት፣ ታዳዎች፣ እና አዋቂቆች ክትባቱን ካገኙ በኋላ እነዚህነ ችግሮች ሊያጋጥሟቸው ይችላሉ።
- ከህክምና በኋላ፣ ክትባትን ጨምሮ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ራሳቸውን ይስታሉ። ለ15 ደቂቃ መቀመጥ ወይም መተኛት ራስን መሳት እንዲሁም በመውደቅ የሚመጣውን ጉዳት ይከላከላል። የድንዛዜ ስሜት፣ የእይታ ለውጥ ወይም ጆሮ ውስጥ ማቃጨል ከተሰማዎት ለሀኪምዎ ይንገሩ።
- አንዳንድ ሰዎች ትከሻ ላይ ከበድ ያለ ህመም ሲሰማቸው የተወጉበት እጃቸውን ማንቀሳቀስ ያስቸግራቸዋል። ይህ አልፎ አልፎ የሚከሰት ነው።

የክትባቶች ደህንነት ሁልጊዜ በቅርብ ክትትል ውስጥ ነው። ለበለጠ መረጃ ይህን ይጎብኙ: **www.cdc.gov/vaccinesafety/**

## 5 | አደገኛ የሆነ የአለርጂ ምልክት ቢኖርስ?

**ማየት ያለብኝ ምንድነው?**
- ስጋት የሆነብዎትን ነገር እንደ **ከባድ የአለርጂክ ምልክት**፣ ከፍተኛ ትኩሳት ወይም ያልተለመዱ ባህርያትን ይመልከቱ።

  የከባድ አለርጂክ ምልክቶች የሚያካትቱት ሽፍታዎች፣ የፊትና የጉሮሮ እብጠት፣ የመተንፈስ ችግር፣ ፈጣን የሆነ የልብ ምት፣ መደንዘዝ እና ድካም ናቸው። አብዛኛውን ጊዜ ከክትባት በኋላ ከትንሽ ደቂቃ እስከ ትንሽ ሰዓታት ይፈጠራሉ።

**ምን ማድረግ አለብኝ?**
- ከባድ የሆነ የአለርጂክ ምልክት ወይም ሊቆይ የማይችል አስቸኳይ ከመሰልዎት 9-1-1 በመደወል አቅራቢያ ወዳለው ሆስፒታል ይሂዱ። ካለበለዚያ ሀኪምዎ ጋር ይደውሉ።
- ከዚያ በኋላ የአለርጂው ምልክት ለ "Vaccine Adverse Event Reporting System" (VAERS) ሪፖርት መደረግ አለበት። ሃኪምዎ ይህንን ፋይል ሪፖርት ማድረግ አለበት ወይም እርስዎ ራስዎ የ VAERS ድህረ ገጽን በ **www.vaers.hhs.gov**, በመጠቀም ወይም በ **1-800-822-7967** መደወል ይችላሉ።

VAERS የህክምና ምክር አይሰጥም።

## 6 | The National Vaccine Injury Compensation Program

የ National Vaccine Injury Compensation Program (VICP) የፌደራል ፕሮግራም ሲሆን በክትባት ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ካሳ የሚሰጥ ነው።

በክትባት ጉዳት እንደደረሰባቸው የሚያስቡ ሰዎች ስለ ፕሮግራሙ ለማወቅ እና መጠየቂያ ለመሙላት በ **1-800-338-2382** ይደውሉ ወይም የ VICP ድረ ገጽን በ **ይጎብኙwww.hrsa.gov/vaccinecompensation**። የካሳ ጥያቄ ለመጠየቅ የጊዜ ገደብ አለው።

## 7 | እንዴት የበለጠ ማወቅ እችላለሁ?

- ሃኪምዎን ይጠይቁ። እርሱ ወይም እርሷ የክትባቱን ማብራሪያ ወረቀት ወይም ሌላ የመረጃ ምንጭን መጠቆም ይችላል/ትችላለች።
- የእርስዎን ግዛት የጤና ዲፓርትመንት ጋር ይደውሉ።
- Centers for Disease Control and Prevention (CDC) ን ያግኙ:
  - **1-800-232-4636** (**1-800-CDC-INFO**) ይደውሉ ወይም
  - የ CDC ን ድረ ገጽ በ **www.cdc.gov/vaccines**ይጎብኙ

Vaccine Information Statement

# Hib Vaccine - Amharic

4/02/2015

42 U.S.C. § 300aa-26

Office Use Only

DCH-0449AM
AUTH: P. H. S., Act 42, Sect. 2126.

Translation provided by Minnesota Department of Health

**የሕክምና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ(ዎች) ትክክለኛ የክትባት ሁኔታ መረጃ እንዲኖራቸው፣ የክትባት ግምገማ፣ እና ለወደፊት ክትባቶች የቀረበ መርኃ ግብር ለመፍቀድ መረጃ ለምችጋን እንክብካቤ ማሻሸያ መዝገብ ቤት** (Michigan Care Improvement Registry) **ይላካል። የሕክምና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪአቸው የክትባት መረጃ ለመዝገብ ቤቱ እንዳያቃብል ለመጠየቅ ግለሰቦች መብት አላቸው።**